# በህገመንግስቱ ጥላ ስር የሚደረግ ትግል ለተረጋጋ የመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲ መሰረት ነው

ሰኔ 18፣ 2002 ኢ.ም

መንግሥት በሀገራችን የሚካሄደውን የሰላም የልማትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት በመምራት ፈጣን ልማትና ብልፅግናን ለመፍጠርና የህዝብን ሰላምና ደህንነትም አስተማማኝ መሰረት ላይ ለማኖር የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትን ማከናወኑ ይታወቃል።

በዚህም ሂደት በህገ መንግሥታዊው ዴሞክራሲያዊ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ውስጥ አላማዎቻቸውን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ የማራመድ ፍላጎት ያላቸውን ወገኖች በማበረታታት በአገር ግንባታው ሂደት ውስጥ የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ሲያመቻች ቆይቷል። በዚህ አሳታፊ ፖሊሲውም የአገራችን ሰላምና ደህንነት አስተማማኝ መሰረት ላይ እንዲቆም ያደረጉ  አያሌ ተጨባጭ ውጤቶችን ማፍራት ችሏል።

በመሆኑም በቅርቡ በሃገራችን የሶማሌ ብሄራዊ ክልል ውስጥ ፍላጎታቸውን በሃይል ለማራመድ ሲሞክሩ ከቆዩ ድርጅቶች መሪዎች ጋር ተቀራርቦ በመወያየት ድርጅቶቹ ህገ መንግስታዊ ስረአቱን ተቀብለው ሰላማዊና ህጋዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋገጠ ስምምነት ተደርጓል። ከጥቂት ወራት በፊት የተባበረው የምእራብ ሶማሌ አርነት ግንባር (UWSLF) በመባል ከሚታወቀው ድርጅት አመራሮች ጋር ተቀራርቦ መነጋገር በመቻሉ ድርጅቱ አላማውን ለማራመድ

የሚጠቀምበትን የሃይል ስልት በመተው በህገ መንግሥቱ ጥላ ስር በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ ያለውን ዝግጁነት በተግባር ማረጋገጡ ይታወሳል ።

ድርጅቱ ለህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ተቀብሎ ሰላማዊና ህጋዊ የትግል አቅጣጫውን ለመከተል በመወሰን የወሰደው ይህ አዎንታዊ ርምጃ የመላ አገሪቱን በተለይም ደግሞ የሶማሌን ክልል ሰላም አስተማማኝ በማድረግ በኩል የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል።

በተመሳሳይ መልኩ ሰሞኑን የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር በሚባለው ድርጅት ውስጥ አብላጫውን አባል ያሰባሰቡ አመራሮች የድርጅቱን የቆየ አመፃዊ የትግል ስልት በመተው በሰላማዊና ህጋዊው መንገድ አላማቸውን ለማራመድ ከመንግሥት ጋር ተስማምተዋል።

ሁለቱ ድርጅቶች በህገ መንግስቱ ጥላ ስር ሆነው አላማቸውን በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ ለማራመድ መወሰናቸው በሶማሌ ክልል በመካሄድ ላይ ያለውን የተፋጠነ የልማት ሂደት በማጠናከር ረገድ ካለው የጎላ አስተዋፅኦ በተጨማሪ በክልሉ ከመቸውም ግዜ የተሻለ ሰላም መስፈኑን አመላካች ነው። አብዛኛዎቹ የኦብነግ አመራሮችና አባላት ለአገራችንና ለክልሉ ልማትና ሰላም መጠናከር ሲሉ የወሰዱት ይህ በጎ ርምጃ ከኤርትራ መንግሥት ጋር በማበር የተለመደ የጥፋት ተግባሩን ለመቀጠል የመረጠውን በድርጅቱ አናሳ አባላት የሚደገፈው አንጃ የሚከተለው የጥፋት መንገድ የማያዛልቀው መሆኑን ጠቋሚ ነው።

መንግሥት በህገ መንግስታዊ ስርዓት ጥላ ስር አላማቸውን ለመራመድ ውሳኔ ላይ የደረሱት እነዚህን ወገኖች ከዚህ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ በመድረሳቸው ያለውን አድናቆት እየገለጸ እንደማንኛውም ዜጋ በህጋዊና ሰላማዊ መብታቸው ይበልጥ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ለማስቻል የሚጠበቅበትን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ያረጋግጣል።

ከመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት